# ወይ ውረድ ወይ ፍረድ

አ ብይ አብይ ብሎ፣ ብዙ ሰው ዘምሮ

ብ ልጣብልጡ ጁዋር፣ አልጋህን ሰርስሮ

ይ ታያል ሲያጠፋ፣ ግብርህን ተፃሮ

አ ዲስ አበባችን፣ የኢትዮጵያ ከተማ

ህ ዝብ ታመሰባት፣ ዙሪያ ገባው ደማ

መ ጤ ነህ ተብሎ፣ ብዙ ሰው ታረደ

ድ ንገት ተፈናቅሎ፣ የትም ተሰደደ

ወ ገንህ አለቀ፣ በኦነግ ቅስቀሳ

ይ ቅርታ መደመር፣ አሳየን አበሳ

ፍ ትህ አይጓደል፣ እውነት ይነገር

ረ ኸሙ ጉዞህ፣ በአጭር እንዳይቀር

ድ ርጊቱ ይወገዝ፣ አገር ማሸበር

ወ ንጀለኛው ሁሉ፣ ለህግ ይቅረብና

ይ ጠየቅ በፍትህ፣ ህዝባችን ይፅናና

ው ስጣችን ሳይጠራ፣ ድምር ስታሰላ

ረ ጋ ያለው ህዝብ፣ በጠላት ተበላ

ድ ፍን አዲስ አባ፣ በጅጉ ተጉላላ

ወ ገን ተጨነቀ፣ በዛ ትርምስ

ስ ንዴን ከእንክርዳዱ፣ ለይ አትታገስ

ን ፁህንን ጠብቅ፣ ፍቅርህን አድስ።

ከዘውዲቱ የማነ

2018-09-24